# ጫንቡሬ ፈረሴ
(ማህሌታዊ ሰመመን)

ዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ

ጫንቡሬ ፈረሴ፣ ጫንቡሬ ጫምቡሬ
የኔ ተፈትላኪ፣ የኔ ቡራቡሬ፣
አንቺን ብዬ ቼቼ!
ቼቼ! ቼቼቼቼ!
ቼቼ! ቼቼቼቼ!
ታውጆ መንጎዴ፣
ልናፈቅ በሁሉ፣ ልባል መጥቶ መቼ፣
ኧረ መቼ መቼ፣ ኧረ መቼ መቼ!
ሃሜትን ሸምቼ
ሸምቼ ሸምቼ
እንዳልቀር ታምቼ
ታምቼ ታምቼ
ልበል ቼቼቼቼ!
ቼቼ! ቼቼቼቼ!

ጫንቡሬ ፈረሴ፣ ጫንቡሬ ጫምቡሬ፣
ሌሎች ቢያንቋሽሹሽ ለኔ ነሽ ክቡሬ፣
አዝለሽኝ ዝመቺ ሳላልቅ ተቦርቡሬ፣
ሲጎሸም ነጋሪት፣ ሲመታ ታምቡሬ፣
ይዘሽኝ ፈትለክ በይ፣
ሁኚና ቅልምልም፣ ሆነሽ ቡራቡሬ፣
ቼ! ልበል ሰባቴ፣ ቼ! ልበል ዐሥሬ፣
በራሤ ገርዳሳ
ወይ ጭንብላ አሥሬ፤፤

በምሽት ጋልቤሽ
ጀምበሯ ተሳክራ ስትሾር ጋራ ላይ፣
እሳትዋን ረጭታበት
ፍም ሲመስል ቀላይ፣
አድማስ ወርቅ ሲለብስ
ለዐይን አማላይ፣
ንፋሱ ሲላፋ ከአበባ ጋራ፣
አበባ ላፍንጫ
ሽቱውን ሲያጋራ፣
እላይሽ መጭ! ብዬ
ልበል ቼቼ! ቼቼ!
ቼቼ! ቼቼቼቼ!
ሃሜትን ሸምቼ
ሸምቼ ሸምቼ፣
እንዳልቀር ታምቼ፣
ታምቼ ታምቼ፣
ልዝፈን ቼቼ! ቼቼ!
ቼቼ! ቼቼቼቼ!

ልናፈቅ በሁሉ፣
ልባል መጥቶ መቼ፣
ኧረ መቼ መቼ፣
ኧረ መቼ መቼ!

በሌሊት ጋልቤሽ፣
እንዳይ ቦቃ ጭንብር፣
ከጨቅላዋ ባቲ፣
ሲፈስ ቀልጦ ብር፣
ጸዳላዊው ዝናብ
ሲያርከፈከፍ ሲረጭ ጨረርን በክብር፣
ጫንቡሬ ጫምቡሬ
ጫንቡሬ ጫምቡሬ
የኔ ተፈትላኪ
ባለክንፏ ፈረስ የኔ ቡራቡሬ፣
ወይ በደንገላሳ አልያም በሶምሶማ
ጫንቡሬ ጫምቡሬ፣
በሽምጥም ካልሽኝ ይዘሽኝ ሽምጥጪ
ሲጎሽም ነጋሪት፣
ሲመታ ታምቡሬ፣
ጫንቡሬ ጫምቡሬ፣
ሌሎቹ ቢደፍሩሽ
ለኔ ነሽ ክቡሬ፣
እባክሽ አልባክን
ውስጤን ተቦርቡሬ፣
ሆነሽኝ ባቡሬ
ሁኚና ቅልምልም
ሆነሽ ቡራቡሬ
ልበል ቼቼ! ቼቼ!
ቼቼ! ቼቼቼቼ!
ቼቼ! ቼቼቼቼ!
ዜናዬ ተበስሮ ሁኜ ተናፋቂ
ልባል መጥቶ መቼ፣
ኧረ መቼ መቼ!
ኧረ መቼ መቼ!
ጫንቡሬ ጫምቡሬ
ጫንቡሬ ጫምቡሬ፣
ባለ ብዙ ቀለም
ኅብረ-ቡራቡሬ፣
ሁኚና ሐምበላይ
ባሕር የሚዳርጥ፣
ቋጥኝ የሚያዶቄት፣ ቀላይን የሚንጥ፣
ፈሳሽን ከጥጥር ከቶ 'ማያማርጥ፣
ወይ ሁኚና ጠሮ
ዛፍ ባሸዋ እሚውጥ፣
ተራራ እሚዳምጥ፣
ሃይቅ እሚበጠብጥ፣ ምድር እሚያናውጥ፣

ሃይቁ ሲንቦቀቦቅ
በአረፋ ድፍቀት፣
በጨረቃ ስበት
ሲንር ወደ ሕዋ፣ በነውጥ በጭንቀት፣
ወይ እሱን አያርገኝ!
ወይ የሱን መጠሪያ!
በውድቅት በውድቅት በወር የሚቀውስ፣
ሆኜ እንዳልቀር እኔም የጨረቃ ባሪያ፣
'ባሕር ልዝለል የምል፣ ወይም ጨርቄን ጥዬ
ልወርውር እንዳልል ከሰማይ-ነክ ጣሪያ፣
ንፋሱ ሲያስካካ እንደ አረር እሩምታ፣
እንዳዳፍኔ ዋይታ፣ እንደ ጅቦች ስሪያ፤
ነፍስ ሲበረብር፣ የውሽንፍሩና ዲናው ጉሩምሩምታ፣
ውሰጂኝ አንጉጂኝ፣ ስልሽ ቼቼ! ቼቼ!
ቼ! ቼቼቼ! ቼ! ቼቼቼ!
ጉዞዬ ተነግሮ፣
ተናፋቂ ሆኜ ስባል መጥቶ መቼ
አረ መቼ መቼ! አረ መቼ መቼ!
መሰስ! ብዬ እንዳይ
ቅልምልም ከዋክብት ሰማይ ሲደረድር፣
ሽረሪት-ከዋክብት..
ብርቅርቅ የአደሩ ያእላፍ ብርሃናት ድር፣
ያቺ ጭንብር ቦቃ
ጨርቃ ጨረቃ
ቀልቤ ሲጠረቃ
ዐይኔ ሲመረቃ፣
ብርቱካን ጨረሯን
ፏፏቴ ላይ ለቃ፣
ለመሆን ሲቃጣት
የጭለማ አለቃ፣
በግሩማን ሌሊት፣
እርጭታው ሲያስፈራ፣
ጓጉንቸር ጸዋ ሲል
ሽብርን ሲያፈራ፣
በብርጉድ፣ ሊባንጃው፣
በከርቤ የሚያውድ፣
ጉም፣ የ 'ጣን ጭስ መስሎ
አፍንጫን ሲሸውድ፣
ይዘሺኝ ተጨለጭ ጫንቡሬ ጫምቡሬ፣
የኔ ተፈትላኪ፣ ፈረስ ቡራቡሬ፣
ሲጎሰም ነጋሪት፣ ሲመታ ታምቡሬ፣
ሌሎች ቢያቃሉልሽ፣
ለኔ ነሽ ክቡሬ፣
ባክሽ ቶሎ ጥፊ ብለሺኝ እንኮኮ፣
ይገፔ ከተፍ ብለሽ፣ ሆነሺኝ ባቡሬ፣
እንዳልጎዳብሽ ብዙ ተቦርቡሬ፣
ልጋልብሽ ሰባቴ፣ ልጋልብሽ አስሬ
ጫንብላም ካልሆነ፣
ገርዳሳ አስሬ።

ጫንቡሬ ጫምቡሬ፣
የኔዋ ቅልምልም፣ የኔ ቡራቡሬ፣
እራስሽ ስሜን ነው፣
ጭራሽም ከደቡብ፣
አንድ ዐይንሽ ዱዳሌብ፣ ሌላኛው ከናጌብ፣
እንታጠቅ ስልሽ አትሁኝ ሆደቡብ።
ልታጠቅ ታጠቂ
ርቀቱን እንመርሽ አይታጠፍ ግንባር፣
አለ ካድማስ ወዲያ ርቀት ስታጠቂ፣
የምንፈጽመው እሪ! የሚል ተግባር።

አንድ እግርሽ ከምዕራብ
ሁለተኛው ምስራቅ፣
ሶስተኛው ከመስእ፣ አራተኛው ባህር፣
ምድሪቱን ከድነሻል ሳትሄጂ በመራቅ፣
ሳትሄጂ ሄደሻል፣
ያልሄድኩ እኔ'ንጂ ነኝ፣
አዝምቺኝ አካሌ
የተጣባኝ አዚም ደብቶ አይጫነኝ።
በሌሊት ጋልቤሽ
እንዳይ ጭንብር ቦቃ፣
ያቺን ብጫ ዶቃ፣
ጭንቡል! ልበል ልብረር አልሆንም ቦቅቦቃ!
ጠላቴ ጨንብሶ
እንዲጨነባበር፣
ፈለጌን ፈልጎ
አትጥቶኝ እንዲሸበር።
ያቺ ብጫ ዶቃ፣
ያቺ ጭንብር ቦቃ ጨርቃ ጨረቃ፣
ማር-አስተኔ ጨረር፣
ሃይቁ ላይጠረቃ
እሃይቁ ላይ ለቃ፣
ሃይቁ ሲሆን ወተት፣
መሆኑ ከጅሏት የሌሊቱ አለቃ
በጠጅማ ጣትዋ ወተትማውን ሃይቅ፣
ሽቅብ እየሳበች ከብራ ሆና ሉሊት፣
በድድቁ ጽልመት፣
በዚያ ባፍላው ሌሊት፣
ደፋር ነኝ በማለት ውሃውን ስትጎትት፣
በኔ አድሮ ጉጉት፣
ላደምጣት ስጣደፍ ጸጥታ ሰንጥቃ
ጭለማን አንዝራ ስታሚርት ጉጉት፣
ሰማይ ሲተረተር የጉጉትዋ ሚርቷ፣
ፈንድቶ እንደ ቡልቃን
የወጣው ከምብርቷ!
ነብር በሽንት ሲሾቅ፣
አንበሳ በቅዘን፣
ያስር ሺ ዓመት ሃዘን፣
ባንድ ሌት ሲታዘን፣

ጫንቡሬ፣ ጫምቡሬ፣
የኔ እብስ! ባይ፣ የንፋስ ፈረሴ፣
የኔዋ ቅልምልም የኔ ቡራቡሬ፣
ሲጎሽም ነጋሪት፣
ስገሪልኝና ሲመታ ታምቡሬ፣
ወይም እንደ በቅሎ እመጭ! ልበልብሽ
ጫንቡሬ፣ ጫምቡሬ፣
ለሌሎች እንጃ 'ንጂ
ለኔ ነሽ ክቡሬ፣
መጭ! ልበል ይዘሽኝ፣
በስጋት ሳልወድም ውስጤን ተቦርቡሬ።
ጭምቡል! ልበል ልብረር
ሆነሽኝ ባቡሬ፤፤

መሻገት ነውና መርጋት ካንድ ስፍራ፣
ይጨናበር ፈላጊዬ ጠፍቶበት ፈለጌ፣
ምንተዳዬ ምንተዳሽ፣
እኔ ለባለጌ፣ አንቺስ ለባለጌ!
ወሬኛ እንዳያማን፣ ከቶም እይገባ--
ለሐጭ ማዝረብረሽ፣ እኔም ማዝለግለጌ።
መዛግ ስለሆነ መቆም ካንድ ስፍራ፣
ይዘሺኝ ንጎጂ ባይኖረኝም አጀብ፣
እኔ እሻልሻለሁ ከጎበዞች ጭፍራ።
መቼ ኖሮት አጀብ ጥንቱንስ አንበሳ፣
ብቻውን አይደል ወይ ሁሉን የሚጋፈጥ፣
ተቆልሎ ቢደርስ መከራና አበሳ?
ለብቻ ተደርሷል ታላቅ እጹብ ድርሰት፣
ለብቻ ተገኝቷል ታላቅ ብርቅ ግኝት፣
ለብቻ ተሰልቷል ያለም ታላቅ ስሌት፣
ለብቻ ተቃኝቷል ታላቅ አዲስ ቅኝት።
በግሉ ነው ወትሮም፣ ልበ-ሙሉ እሚጓዝ
ለብቻው ነው ጥንትም የሚሽፍት ጎበዝ፣
በርሃ 'ሚደፍር
'ዱር የሚቅበዘበዝ።
አንድ ነፍሱን ሆኖ ደፋር የነደፈው
ለብዙኀን ተርፎ እስከሚተገበር፣
ባለም እስኪዛመት፣
ያንድ ራዕይ ሆኖ ይቆያል በ ዝግ በር።

አንድኮ ነው ሁሌም፣ አልሚ ወይም አጥፊ፣
አንድኮ ነው ድሮም፣ ሰውን የሚያድነው ወይም የሚገድል?
አንድ አይደል የሚፈርድ ወይ የሚገመድል?
አንድ አይደለ አብቂው፣ ለሽንፈት ወይ ለድል?
ሌላውስ ጀሌ ነው፣ የጭፍን ተከታይ፣
ሆ! ሲሉት ግር! የሚል፣ ተነጅ ተግተልትሎ፣
አድርግ ሲሉ 'ሚያደርግ፣ “ለ'ንጀራዬ” ብሎ።
አንድ ቀና መሪ፣ ይስጥሽ አንድ ሃቀኛ፣ እሱን ተከትሎ
ሕዝብሽ እንዲቀና በመሆን ሃቀኛ፣ በውነት ተንበልብሎ፣
የሱን አርአያነትከልብ ተቀብሎ።

ልክ እንደመሪው ነው፣
እሚሆን ተመሪ፣
እመኚኝ እውነት ነው
ይህንን የኔን ቃል ብትመራመሪ።

“ብዙሃን! ብዙሃን! ብዙሃን! ብዙሃን”
ተብሎ ሲፎከር ብዙ 'ሚጋነነው፣
በበዙሃኑ ስም መሸቀጥኮ ነው!!!!
“ወሳኝ ብዙሃን ነው፣” ሲባል የሰማነው፣
ባዶ ቀረርቶ ነው፣ ነቅቶ ለሚያጤነዉ፡
ማን ወሳኝ እድርጎት፣ ወሳኙስ አንድ ነው።

ይህንን መልክቴን፣ ትገንዘበው ፍቅሬ፣
ንገሪያት ፈረሴ፣ ጫንቡሬ፣ ጫምቡሬ፣
ከ'ግር እስከ 'ራሴ፣ ባንቺ ተሸቀርቅሬ፣
እላይሽ ረክቤ፣
ቼቼ!! ቼቼ! ቼቼ! እላለሁኝ ቼቼ1
ታማኝነትሽን ካንቺ ተረክቤ፣
ጫንቡሬ፣ ጫምቡሬ፣ ታዛዥዋ ፈረሴ፣
አየሩን ልዋኘው ባንቺ ተንከብክቤ።
ተናፋቂ ሆኜ ሲሉ ደርሶ መቼ፣
ኧረ መቼ መቼ፣ ኧረ መቼ መቼ፣
'ላይሽ ጉብ! ብዬ፣ እያልኩሽ ቼቼቼ!
ቼቼቼቼ! ቼቼ! ቼቼቼቼ!ቼቼ!
እባክሽ ጫንቡሬ፣
ጫንቡሬ፣ ጫምቡሬ፣
ሌሎች ቢያንቋሽሹሽ
ለኔ ነሽ ክቡሬ፣
የኔዋ ቅልምልም፣ የኔ ቡራቡሬ፣
ይዘሽኝ አምልጪ ሲመታ ታምቡሬ፣
በብካይ መንቆሮች፣ በሰቆቃ ጥፍሮች..
ሳላልቅ ተሰርስሬ፣ ሳልረግፍ ተቦርቡሬ፣፣
እብድ ሀሙስ 'ለት ሰዎች፣
እያወቁ-አበዶች ሆነው እንደ ነበር፣
የልብን ለማድረስ፣ ምኞት ለመፈጸም፣
እኛም እስቲ እንበድ፣ አውቀን ጥሰን ድንበር።
ከፍ ስትይ፣ ብዬ ከፍ፣
ዝቅ ስትይ፣ ብዬ ዝቅ፣
የተቃጠለውን አየር ወናፍቼ፣
ትኩሱን፣ አዲሱን፣ በሳምባዬ እንድዝቅ፣
እመር! ሥትዪ፣ እመር! ብዬ፣
ስትነጥሪ ነጥሬ፣
ሥትረዝሚ ረዝሜ፣
ሥትአጥሪ አጥሬ፣
ስልትሽን አስልቼ፣
የ'ንቅስቃሴሽን፣ ፍጹም ግጥማዊ ምት፣
ግጥማዊ እድርጌ እንዳንቺው መትቼ፣
በጋላቢ መላ፣ በደመ-ነፍስ ግምት።

በደረቁ ውድቅት
ውሾች ሲያላዝኑ፣
”ካንዱ ቤት አንድ ሰው፣
“ሚች ነው!” ብለው ሲያዝኑ፣
”ትልቅ ሰው ሊሞት ነው!”
እያለ በ'ሬታ ሲገነደስ ወርካ፣
ተፈጥሮ ሲያሚርት፣
የገደል ማሚቶ ሆና የሱ ሽርካ፣
የሰማዩ ላይ ጥጥ ነዲድ ሆኖ ጋይቶ፣
ፀሀይን አሳዶ እቶኑ እንዳይበላት፣
አጽናፉ ሲያሸሻት ነበልባሉን ዐይቶ፣
የጭራቆች ተረት
በጽልመት ሲተረክ፣
ጽልመትየው ራሱ
ፈርቶ ሲብረከረክ፣
ዘጠኝ-ዐይናው ጭራቅ፣
ሲገንን በመድረክ፣
እኔን ይዘሽ ፈትለክ፣
ያንቺ ለጋ ጉልበት፣ ሳይል ሽበረክ! ሽብረክ!
ስለዋልሽልኝም አይከፍሉት ውለታ፣
ብሩኩ ሕይወትሽ፣ ዳግም እንዲባረክ::
ጫንቡሬ፣ ጫምቡሬ፣
ጫንቡሬ፣ ጫምቡሬ፣
የኔ ተፈትላኪ፣
የቅጽበት ባቡሬ፣
ሲጎሽም ነጋሪት፣ሲመታ ታምቡሬ፣
የኔ ባለ-ቀለም፣
የኔ ቡራቡሬ፣
ይዘሽኝ እልም! በይ
ሳላልቅ ተቦርቡሬ::

ሰማይ በፍንዳታ
ሲቃጠል ብቡልቃን፣
ለሃጥዐን በመጣው
ሲጋዩ እነጻድቃን፣
ሌሊቱ በሁከት፣
በርደት ሲል እረጭ!
አልሞት-ባይ ተገዳይ
ጃርት እሾህ ሥትረጭ፣
ዘንዶ ተጠምጣሚ
በዛፍ ሲጠማጠም፣
አዳኝና ታዳኝ
ባንድ ሲገጣጠም፣
እባብ ሰለክላኬ፣
አያ ሾለክላኬ፣
በካብ ሊስለከለክ፣
ጫንቡሬ፣ ጫምቡሬ፣
በዱር አራዊቶች አንበሳ ሲመለክ፣
ሳተና ፈረሴ፣ የኔ ቡራቡሬ፣

ያኔ ነው መፈትለክ!!
ጫንቡሬ ጫምቡሬ!!
ያኔ ነው መሽሎክለክ!!

ከ'ባብ የባሰች ጊንጥ፣ ግዙፍ ዘንዶ ነድፋ፣
አሸዋ ውስጥ ሰምጣ፣ በ'ባብ ሰለክላካ
የመርዝ ደባዋን፣
ሽምጥጥ! አርጋ አላካ፣
ውዮ! የግፍ፣ የግፍ!
ያላግባብ ያላግባብ፣
ምስኪኑን ልታስውጥ
በሰበብ በአስባብ፣
እኩዩን ስራዋን
ስትለጥፍ በእባብ፣
የጊንጧ ሲያስደምም፣
ደሞ ዳሞተራ፣
ከፍታ ከደብተራ፣
አንበሳን ስትነክሰው
ባለግርማን መድፈር ሆኖ የሷ ተራ፣
ሌሊቱ ተላብሶ አእላፍ ትላበራ፣
ምዕልፊት ከዋክብት የረገፉ መስለው
ብልጭልጭ! እያለ መሬቱ ሲያበራ፣
ሠማይ ተንደርክኮ-- ጸሃያቱ ሮማን-ቀይ በስለው፣
ምናውዬ የዱ፣ ገብታ በዝሆን ቂጥ፣
በጣጥሳ፣ ዘንጥላ፣ በልታ ሆድዕቃውን፣
በቁም ስትጨርሰው፣
ዝሆን ያለ መስሎት፣ አለሁኝ ሲል በውን፣
"በፊት የማትገጥመው
"ከሁዋላ ረታቺው፣
"ቦቅቧቃ ወኔዋን
"እያበረታቺው::
"በስተጀርባ ማጥቃት
"የፈሪ ጸባይ ነው የኖረ ዘላለም፤
"ጀግና ፊትለፊት ነው
"ወትሮም የሚፋለም፤
"በፊትለፊትማ ዝሆንን ማ ገጥሞ፣
"ከሁዋላ ሆኖበት፣
"በአልባሌ የዱ፣ ቀረ ተቆርጥሞ!"
ተብሎ ሲለቀስ--
"ተብረከረከ ያ ዝሆን!
"ተብረከረከ ያ ዝሆን፣
"አንበሳ-ሰገድ ምን ሆኖ ይሆን?
"ተብረከረከ ያ ዝሆን፤፤
"ፈሪና ተራራ ባንድ ሃሳብ ይኖራል፣
"ጀግና ብርሌ ነው፣ ወድቆ ይሰበራል!
"ጎበዝ ይኑር እንጂ፣ ፈሪ ይሙት ቢሻው፣
"አተላ መሸከም ይወዳል ትከሻው!"

ታዲያ ያኔ በተረከዜ
እኔ ሆድሽን ስኮረኩር፣
ወዳየር ነፉሪ
ሁኚ መንኮራኩር፤፤
ዐለም ከጠበበን፣ ሽቅብ እንተኮስ
ከከዋክብት በላይ፣ ከአርያም በታች
ሽቅብ ነጣቂ 'ንጂ፣
ሳይኖርብን ጎታች::
ናብሊስ አጥልቄልሽ አንገትሽን አስውቤው፣
ነቤላ እየበላሽ ናብሊልኝ ወደላይ፣
ናብሊስሽ ይናብልስ፣
ከአምባ ተራራ፣ ከኩሬ እስከ ቀላይ፤፤
ናብሊስ አስናቂ ነው፣
ከመረሻትና ደሞ ከሻሁራ፣
መረሻት አድራጊ ካንቺ ቢወዳደር፣
ጫንቡሬ አትጠርጥሪ፣ ወጪኮ ነው ሁራ፤፤

ምናምንቴ የሎስ፣ በሬ አንጠልጥሎ
እንደ ጢንቸል ሁሉ፣ በሬ ሲንፈራፈር፣
አጀብ ነው! ዕጹብ ነው! በሬ ሲሆን ድምቢጥ!
ጉድኮ ነው ላድማጭ፣ አስፈሪ ሲደፈር፤
በዘመን ግርምቢጥ!
ነገር አይሆን ሆኖ እየለቀቀ ፈር፣
ባህር ድል ተመቶ
ሆኖ እንደ አፈር፣
ለሰሚው ግራ ነው፣
በወንፊት ሲሰፈር!

“ዬ! ዬ! ዬ!… ዬ! ዬ! ዬ!…
“አዬ! አዬ! አዬ!… አዬ ጊዜ! አዬ ዘመን!”
እያልኩ ከማነባ
ወቅቱ ሆኖ የማይታመን፣
ይዘሽኝ ክነፊ ጫንቡሬ ጫምቡሬ!
ጫንቡሬ፣ ጫምቡሬ፣
መሸሻዬ ፍቅሬ
ጎብረ-ብራቡሬ!
በኔ አልተጀመረም
ከሰቆቃ መሸሽ፣
“ፈሪ ነህ!” ካልሽም በይ፣
ታክቶኝ ባረግ ገሸሽ::
ብዙም ሥንቅ አልሻም፣ እኔ ለመንገዴ፣
ይብቃኝ አበቡቴ፤
አበቡቴም ካጣሁ፣
ልጥገብ በባቡቴ::
ብቻ ቱር! በይልኝ፣ አንቺዬ በሞቴ፤
ወደ ኋላ ብለሽ ዘግይተሽ ፈረሴ፣
በከንቱ አይፍሰስ የፈላው ሃሞቴ::

ምስኪኗን ወዳጄን ሆኖም አስጠንቅቂያት-
ውድሽ እንዲህ ብሏል እባክሽን በያት፣
ጆሮሽን ከፋፍተሽ ካደመጥሽው ምክሬን
የመጠቀ እኮ ነው፣ ከሰማይ ሰማያት--
አንዱን ቀዳዳሽን ስትጥሪ ልትደፍኚ፣
እንዳይተካው ሌላ እንጦርጦሳዊ ብስ፣
ይሻልን ስትፈቺ ደምሽ ነፍሮ ነፍሮ፣
ብቻ እንዳያገባሽ ያልጠበቅሽው ይብስ!!
በዘነበ ቁጥር በተንዶለዶለ
የግፍና በደል ወጨፎና ዝናብ--
አይቀርም መምጣቱ ጠራርጎ ወሳጅ ጎርፍ፣
እውቅ እውነት ነው ይኼ፣ ከቶም አደል ምናብ፡፡
ይዋል ይደር 'ንጂ የማታ 'ማታማ
ፈረሰኛ ጋልቦ መድረሱ አይቀር ጎርፉ፣
አብሮ መሾቅና መጨቅየቱ ሳያንስ፣
ዋ! አብሮ መጠረግ፣ ብቻ እንዳይሆን ትርፉ!!

ለጊዜው፣ እጅሽን አጣጥፈሽ ከምታይ፣
ሰንሰለቶችሽን ልትበጥሺ ጥረሽ፣
በርቺ ተበራቺ ቀንበርሽን ለመጣል
ከጀርባሽ አውርደሽ፣ ከጫንቃ አሽቀንጥረሽ!
ካልተላወሽማ፣ ካልተንቀሳቀስሽ፣
"አክትማለች በቃ!" እነሱ ይሉሻል፤
ስለዚህ ፍቅርዬ ቢሆንም፣ ባይሆንም
በድን እንዳትባይ፣ መንቀሳቀሱ ነው ልምከርሽ የሚሻል፡፡

በጥንት በጠዋቱ፣ ካመጸኛ ሰዎች ዲያብሎሱ ነጥቆ፣
ያመሳቀላትን፣ ይችን የቀወሰች፣ ብጥብጥ የፍዳ ዓለም፣
ዓለሚቱን ሠሪው፣ እራሱ ወደፊት መጥቶ እስከሚመራት፣
ፍጹም ሰላም፣ ፍቅር፣ ፍትህም ነጻነት፣ይሄ ሁሉ የለም፡፡
አትጓጊ እምብዛም እኚህን ለማግኘት
ከእኩዩ፣ እቡዩ፣ ከዛ ከጨቅ ከ ሰው፤
መሰሪ ባህሪው ስለማይፈቅድለት፣
ይህን ሁሉ ላንቺ ወዶ እንዲለግሰው፤
ምን ጭምብል ቀይሮ፣ አዋጆች ቢያንጋጋ
ሺ ቀለም ለቅልቆ፣ ውጭውን ቢያድሰው፡፡

ዳሩ ልውውጡ፣ ያ ግርግሩማ፣
ስለሚፈነጥቅ ጭላንጭሉን ተስፋ፣
በውቅቱ ግርግር ፈንጥዥበት ትንሽ፣
በዝውወሩም ቀን ተስፋሽ ጥቂት ይስፋ!
ዋናው ቁም ነገር ግን፣ በያት የኔን ፍቅር-
አደራሽን ውዴ፣ ራስሽን ሳትደልዪ፣
ምሕላ ስትይዢ፣
'የባሰ አታምጣ' በማለት ጸልዪ፡፡
"ከዚህስ የባሰ ምን ይመጣል!" ስትይ፣
አልነበረም እንዴ የመጣብሽ ይብስ?
ስለዚህ  ጸልዪ እንዳይመጣ ይብስ፣
ይኼኛው ሰዓቱ፤ ቃጭሎበት ሲል እብስ!

በኑሮሽ ላይ ብዙም ግሩም ለውጥ ባይኖር፣
ላንድም ሰአት ቢሆን፣ የግርግሩማ ደስ ይላል ሂደቱ፣
በደል መበቀሉ፣ የላዩ ታች ሆኖ አዲስ ፊትማየቱ፣
እምቁ ፈንድቶ፣ ቁጣ ማስተንፈሱ፣ ያረካል ዕብደቱ::
በተረፈ፣ "ሺ ቢታለብ"
እንዳለችው ድመት "ለኔ በገሌ"፣
ድንቅ ተዐምራት አትጠብቂ
ካዲሶቹ አላቢዎች፣ ደሞ ከነ እገሌ::

የኔ ዐይነቱማ፣ ሊያይ ናፍቆ በጉጉት፣ ፍቅርና ሰላም፣
ፍትህና ነጻነት፣ ፈንታና ዕድልሽን፣ያንቺን መልካም ዕጣን
ከመመኘት በቀር፣ ፈጽሞ የሌለው አንዲት ህቡዕ እቅድ፣
የበይ ታዛቢ ነው፤ ቋቅ! እስኪለው ውጦ፣ በዪ ሲያዝ ቁንጣን::
ይህንን ብለሻት፣ ፍቅርዬን ነግረሻት፣
እስክዛው ግን እኔን፣ ጫንቡሬ፣ ጫምቡሬ፣
ጫንቡሬ ፈረሴ፣ ጫንቡሬ፣ ጫምቡሬ፣
ከመብረቅ ፈጣኗ፣ የኔ ቡራቡሬ፣
ከድምጽ ጥድፏ፣ ጫንቡሬ፣ ጫምቡሬ፣
ይዘሽኝ ቅዘፊ፣ እግርሽን መቅዘፊያ
ጠፈሩን ባር አርገሽ፣
ያየር-መርከብ ሆነሽ፣ አርቂኝ በጥድፊያ!
ጫንቡሬ፣ ጫምቡሬ፣
ጫንቡሬ፣ ጫምቡሬ፣
ሽልምልም ፈረሴ፣ የኔ ቡራቡሬ፣
ሲጎሽም ነጋሪት፣
ሲመታ ታምቡሬ፣
ሌሎች ቢያዋድቁሽ
ለኔ ነሽ ክቡሬ፣
እንዳልመናምን
ውስጤን ተቦርቡሬ፣
ይዘሽኝ ንፈሪ፣ ስገሪ! ስገሪ!
ወይም ሆነሽኝልኝ የሰማይ ባቡሬ፣
ይገፄ ከተፍ! በዪኝ፣
ጎብረ-ቅልምልሚ የኔ ቡራቡሬ፣
እስክመለስ ድረስ...
ታማኟ ፈረሴ ጫንቡሬ፣ ጫምቡሬ፣
ጫንቡሬ፣ ጫምቡሬ፣
ምንም አሁን ብነጉድ
ሰቆቃ ሽርሽሮኝ፣
እመለስ ይሆናል
ብካዬ አሽሮኝ::
ይህ እስከሚሆን ግን፣
"አንት ያገሬ ውሃ፣
"እረንጓዴ አትልበስ
"እጠጣህ የለም ወይ
"ምናልባት ብመለስ::"...

(እአአ 5/10/09 ቫሌሆ፣ ካሊፎርኒያ)

ጣሚው ዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ፣ የ The Hidden and Untold History of the Jewish People and Ethiopians, ደራሲ ነው:: እሱ የሚገኝበት ኢሜል *ftolossa@aol.com* ነው:: በዚህ፣ እላይ ባሰፈረውም

ግጥሙ፣ “ወፌ-ያሬድ” በተሰኘው ሌላ ግጥሙ ላይ እንዳወጀው ሁሉ፣ የራሱን አይነት የቤት አመታት ስልቱን ጠብቋል፡፡ የእሱ የ ግሉ የሆነው አዲስ የግጥም ስልት ምን ዓይነት ሰለ መሆኑ፣ብእዚህኛውም ሆነ በእዛኛው ገጥሙ ያንጸባረቃቸውን የቃላት አመራረጥ፣ የቋንቋ ውበት፣ የሃሳብ ምጥቀት እና ይስሜት ጥልቀት ምንኛነት፣ ስነግጥምን ጠንቅቀው አውቀው ለሚመረምሩ ጠበብት ይተዋል፡፡ ፍቅሬ ቶሎሳ ከአስራ ሰባት ዕድሜው ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የጻፋቸው ገጥሞች እጅግ በርካታ ቢሆኑም፣ የተወሰኑትን ብቻ በአውሮፓና አሜርካን ሬዲዮኖች ከማስደመጡ በቀር ለኢትዮጵያውያን አንባብያንን ያስነበባቸው በጣም ጥቂቶቹን ብቻ ነው፡፡ የእዚህ እንደኛው ምክንያት፣ አብዛኛውን ህይወቱን ከኢትዮጵያ ውጭ ማሳለፉ ነው፡፡ ሁለተኛው በቸልተኝነቱ ነው፡፡ በየ እለቱ ኑሮውን ሲኖሩ ግጥሙ እንደወረደለት እፊቱ ባገኘው ማንኛውም ወረቀት ላይ ከማስፈር በቀር በአማርኛ ለማሳተም አልተጋም፡፡ በጀርመን፣ እንግሊዝ እና ሩሲያ ቋንቋዎች ግን በመጽሃፍ፣ በሬዲዮ እና ባደባባይ እቅርቧቸዋል፡፡ ለወደፊቱ ግን በአማርኛ በመጽሃፍ መልክ ሊያሳትማቸው ለራሱ ቃል ገብቷል፡፡ እስከዛው ድረስ ግን፣ ነሸጦ! ሲያደርገው እንደዚህ ጣል ጣል የሚያደርጋቸውን ግጥሞቹን ለአንባብያን ይጋብዛል፡፡ ግጥሞቹን ቶሎ ቶለ ለማንበበ የሚወዱ ሁሉ፣ ቶሎ ቶሎ እንዲነሽጠው ይጸልዩ፡፡